# ባንኩ የወርቅ አምራቾችን ለማበረታታት ከዓለምአቀፍ ገበያ የ35 በመቶ ጭማሪ አድርጎ ለመግዛት ወሰነ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ አምራቾችን ለማበረታታት በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው የወርቅ ገበያ ዋጋ ላይ የ35 በመቶ ጭማሪ አድርጎ ለመግዛት መወሰኑን አስታወቀ።

ባንኩ ዛሬ በሰጠው መግለጫ እንዳስታወቀው ይህንን ውሳኔውን ከነገ ሰኔ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የከረንሲ ማኔጅመንት ዳይሬክተር አቶ አበበ ሰንበቴ ዛሬ በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፣ ውሳኔው የሚመለከታቸው የባህላዊ መንገድ ወርቅ አምራቾችን ነው።

የወርቅ አምራቾችን ለማበረታታትና የኮንትሮባንድ ንግዱን ለመቆጣጠር ቀደም ሲል የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን ያስታወሱት አቶ አበበ፣ ባንኩ ወቅታዊ ሁኔታዎችን ባገናዘበ መልኩ ከወርቅ አምራቾቹ በሚያበረታታ መልኩ ግዥ ሲያከናውን መቆየቱን ገልጸዋል።

ከመጋቢት 2012 ዓ.ም ጀምሮ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቀው የወርቅ ገበያ ዋጋ በላይ አምራቾች እንደሚያቀርቡት የወርቅ መጠን የሚሰላ ከአስር በመቶ እስከ 29 በመቶ ጭማሪ በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይገዛቸው እንደነበር አስታውሰዋል።

ይህም በመሆኑ በሚያበረታታ መልኩ የወርቅ አቅርቦት ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሲመጣ ቆይቷል ያሉት አቶ አበበ፣ ወርቁም ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ተደርጎ ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት መቻሉንም አስረድተዋል።

ይሁንኑ አጠናክሮ ለመቀጠልና እስካሁን በተለያየ መጠን ለሚቀርብ ወርቅ ይደረግ የነበረውን የተለያየ ማበረታቻ አሁን ወጥ የሆነ ማበረታቻ በማድረግ የተሻለ የወርቅ አቅርቦት እንዲገኝ የሚያስችል አሠራር መከተል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም ከነገ ሰኔ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ከ50 ግራም ጀምሮ ወርቅ ለሚያቀርቡ አምራቾች በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው ዋጋ የ35 በመቶ ጭማሪ አድርጎ ለመግዛት መወሰኑን አቶ አበበ ሰንበቴ አስረድተዋል።